ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ
አውቃፍ ሚኒስትር

ዙልሒጃ 15/1440 ሂ.
ኦገስት 16/2019 ግ.

# ከሐጅ በኋላስ?

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**إِنَّ الَّذِينَ قَالُوا رَبُّنَا اللَّهُ ثُمَّ اسْتَقَامُوا تَتَنَزَّلُ عَلَيْهِمُ الْمَلَائِكَةُ أَلَّا تَخَافُوا وَلَا تَحْزَنُوا وَأَبْشِرُوا بِالْجَنَّةِ الَّتِي كُنْتُمْ تُوعَدُونَ}**

ለአለው ለአላህ ይገባው ትርጉሙም (እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ ከዚያም ቀጥ ያሉ፣ አትፍሩ አትዘኑም በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ፡፡ በማለት በነሱ ላይ መልአከት ይወርዳሉ) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም በተከበረው ሓዲሳቸው (አንድም በአላህ ባሮች ላይ የሚነጋ ሌሊት የለም ሁለት መልአኮች ወርደው አንደኛው : ጌታዬ ሆይ ለጋሽን ሰው በለገሰው ነገር ምትክ ስጠው ሌላኛው ደግሞ ጌታዬ ሆይ ግነዘቡን ጨምድዶ ያዘን ሰው ጥፋትን ፍረድበት የሚሉ ቢሆን እንጂ)፡፡ ያሉት ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

በፍጥረታቱ የአላህን ህግ የሚመራመርና የሚያስተነትን ሰው ቀናት፣ ወራትና ዓመታት በፍጥነት ሲያጓዙ ያያል፡፡ እንዲሁም ዓመታት ዓመታትን ሲተኩ ያስተውላል፡፡ ይህም የሚያሳየው የዚህች ዓለም ሕይወት አስከተወሰነ ጊዜ የሚዘልቁ ጥቂት እስትንፋሳት እንጂ ሌላ ነገር አይደለችም ማለትን ነው፡፡ ይህመ ታድያ ለሚገመግምና ለሚያስተውል ሰው ታላቅ ተግሳጽ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡ وَهُوَ{ الَّذِي جَعَلَ اللَّيْلَ وَالنَّهَارَ خِلْفَةً لِمَنْ أَرَادَ أَنْ يَذَّكَّرَ أَوْ أَرَادَ شُكُورًا}.

ትርሙም (እርሱ ያ (ያመለጠውን ሥራ ) ማስታወስን ለሚፈልግ ወይም ማመስገንን ለሚፈልግ ሰው ሌሊትንና ቀንን ተተካኪ ያደረገ ነው) ማለት ነው፡፡
ከአላህ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ሐጅ በሱ አላህ (ዐ.ወ.) ወንጀልን የሚምርበትና ሰውየው እናቱ እንደወለችው ሆኖ የሚመለስ መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.)እንድህ በማለት አብሰረዋል ከተባለ፡ (የሐጅን ሥራ ጽያፍ ቃል ሳይናገርን አመጽን ሳይፈጸም ያከናወነ ሰው እናቱ እንደወለችበት ቀን ንጹህ ሆኖ ይመለሳል) ልበኛ ሰው ይህን መልካም አጋጣሚና የአለህን ታለቅ ችሮታ በመጠቀም ከሌሎች ወንጀሎች አጥብቆ መራቅና በንጽህ ልብና በታላቅ ተማኝነት ወደ አላህ መፋጠጥ ይኖርበታል፡፡

ይህን የሐጅን ሥራ ያከናወነ ሰው አላህ (ሰ.ወ.) ይህን ታለቅ ዒባዳ በተሳካ ሁኔታ እንዳከናውን ስኬት ስለለገሰው የአላህን ታላቅ ተድላ በልቦናው ሊያስታውስ ይገባል፡፡ እንድሁም ይህ ተግባር በመልካም ሥራ በመዘውተር የአላህን ምስጋና ግድ የሚል መሆኑንም መገንዘብ አለበት፡፡ ምክኒያቱም የአላህ ዒባዳ በተለየ ዘመንም ሆነ ቦታ አይወሰንም፡፡ የአላህ ዒባዳ አንድ ሰው ስትንፋስ አስካለውና የግዴታ መስፈርቱ እስካለ ድረስ የሚዘልቅ ተግባር ነው፡፡ ይህ የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፈለግ ሲሆን እንድህ የሚለውን የአላህን ቃል መሰረት በማድረግ ነው፡

{وَاعْبُدْ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأْتِيَكَ الْيَقِينُ}

ትጉሙም (እውነቱም (ሞት) እስከሚጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ፡፡) ማለት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህም ይላል፡

{فَإِذَا فَرَغْتَ فَانصَبْ ۞ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَارْغَبْ}

ትርጉሙም (በጨረስክም ጊዜ ልፋ፡፡ ወደጌታህም ብቻ ከጅል፡፡) ማለት ነው፡፡
ይህን ማለትም አንድን ዒባዳና ትእዛዝን ስትጨርስ የአላህን ውዴታ በመፈለግ ሌላን ዒባዳና ትእዛዝን እንደገና ጀምር ማለት ነው፡፡ በመልካም ሥራ መዘውተር አላህ (ዐ.ወ.) እጅግ ከሚወዳቸው ዒባዳዎች አንዱ ሲሆን የመጨረሻ ማማር ምልክትም ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ ብለዋል፡ ‹ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ቀን አላህ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆነው ሥራ የተኛው ነው ተብለው ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ዘውታሪ የሆነው ነው፣ ቢያንስም እንኳ፡፡) በማለት መለሱ፡፡›
እንድ ሰው አላህ ዒባዳን ያሳካለት፣ ሥራውን ያሳመረለት፣ ጠባዮን ያበጀለት ከሆነና የሰዎችን ጉዳይ ለማውጣት የሚጥር፣ ከነሱም ጭንቀትን የሚያቃልል፣ በማህበረሰቡና በመላ ሀገሩም መልካም ነገሮችን ለማስፋፋት የሚደከም ከሆነ ምንኛ እድለኛ ነው፡፡
አንድ ምእምን የሀጅን ሥራ በተሳካ ሁኔታ እንዳከናውን አላህ (ዐ.ወ.) ስኬትን የቸረው መሆኑ የዒባዳ መጨረሻ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ወደአላህ (ሱ.ወ.) የሚቃረብባቸው በፈቃድ የሚፈጸሙ አያሌ የስግደትና የጾም ዒባዳዎች እንድሁም እንደየሰዎችና የሀገርን ጥቅም ማስከበር፣ የሙታንን ልጆች መንከባከብ፣ በሽተኛን

መጠየቅና የመሳሰሉ አላህ ዘንድ ደረጃውን ከፍ የሚያደርጉ ዒባዳዎች አሉ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ብለዋል፡ ‹የአላህ መልክተኛ እንድህ ኣሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡ (… አንድ ሰው እኔ በሱ ላይ ግድ ካደረግሁበት ነገር የበለጠ እኔ ዘንድ ውድ በሆነ ነገር ወደኔ አይቃርብም፡፡ አንድ ሰው ግድ ባልሆኑ ዒባዳዎች ወደኔ ማቃረብን ሲያዘወትር ከኔ ወዴታን ያገኛል፡፡ እኔ ከወደድኩት ደግሞ በሱ የሚሰማበት መስሚያው፣ የሚያይበት ማያው፣ ሁሉን ነግር የሚያከናውንበት እጁና የሚራመድበት እግሩ እሆናለሁ፡፡ ከዚያም ቢጠይቀኝ እሰጠዋለሁ፡፡ በኔም ከሰይጣን ከተጠበቅ በእርግጥ እጠብቀዋለሁ፡፡)›

አንድ የሐጅን ሥራ አከናውኖ የተመለሰ ሰው በመልከም ፀባዩ. ሰዎች ጋር ሲዋዋልም ገራገር በመሆኑ የሐጅ ሥራ ገጽታ መታየት ይኖርበታል፡፡ ይህም ታድያ ሐጁ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ያንጸባርቃል፡፡ ከዚያም አልፎ ከዚያ ከሀጅ በፊት የነበረውን የዒባዳ መጓደል ማካካስ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ሁሉ በግልጽ የሚታየው እንደአባት እናት ሚስት ወይም ባል ጋር በአላው የቤተሰቡ ግንኙነት ዓይነት፣ በዝምድና ቅጠላውና በመሳሰሉ ከሰዎች ጋር በአሉ መልካም ግንኙነቶች ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

{ لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَى حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَاهَدُوا وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ أُولَئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ }.

ትርጉሙም ( መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደምስራቅና ወደምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመልአክትም፣ በመጽሐፍትም፣ በነብያትም ያመነ ሰው፣ ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች፣ ለምስኪኖችም ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቂያ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር፣ በበሽታና፣ በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን) እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡

የሐጅ ተግባራት በሰውዬው ላይ የስነ ምግባርና ሰርኣት ተጽእኖ ማሳደር ይጠበቅበታል፡፡ ሐጀ ያለዓላማና የያለግብ የሚፈጸም አምልኮ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሰውን ልጅ ደረጃ ከፍ ለማድርግ ጠባዩን ለመግራት የተደነገገ ዒባዳ ነው፡፡ አላህ እንድህ ይላል፡

{ الْحَجُّ أَشْهُرٌ مَعْلُومَاتٌ فَمَنْ فَرَضَ فِيهِنَّ الْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي الْحَجِّ وَمَا تَفْعَلُوا مِنْ خَيْرٍ يَعْلَمْهُ اللَّهُ وَتَزَوَّدُوا فَإِنَّ خَيْرَ الزَّادِ التَّقْوَى وَاتَّقُونِ يَا أُولِي الْأَلْبَابِ}

ትርጉሙም (ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው፡፡ በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም፡፡ ከበጎ ሥራ አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ያውቃል፡፡ ተሰነቁም ከስንቅም ሁላ በላጩ ጥንቃቄ (አላህን መፍራት) ነው፡፡ የአእምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ ፍሩት፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችንም እንድህ ብለዋል፡ (ወደዚህ ቤት መጥቶ ርኩስ ቃል ሳይናገርና ሳያመጽ የሐጅን ሥራ ያከናወነ እናቱ እንደወለደችው ንጹህ ሆኖ ይመለሳል፡፡) ሐሰን ኢል በስሪ የተሰኙት ሊቅ ተቀባይነት ያለው ሐጅ ምንዳ ጀነት ብቻ ነው፡፡ የዚያም ምልክቱ ሰውዬው ከሀጅ በኋላ መጭውን ዓለም በመፈለግ ለዚህች ዓለም ምንም ዓይነት ትኩረት የማይሰጥ ሆኖ መመለሱ ነው፡፡ ሌላ ከዚህ በፊት የሚሰራቸውን ወንጀሎችን የሚተው ከሆነ የምህረት ሐጅ መሆኑ ነው፡፡› ብለዋል፡፡

ማንኛውም ዒባዳ የአንድን ሰው ጠባይና አጠቃላይ አመሉን የማይቀይርለት ከሆነ በዚህች ዓለም ፍሬ አልባ እንደሁም በመጭውም ዓለም ዋጋ ቢስ ይሆናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድ ቅን እንድህ በማለት ተጠየቁ፡ (ድሃ ማለት ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን? ) እነሱም ከኛ ድሃ የምንለው ብርና እቃም የሌለውን ሰው ነው፡፡ እሳቸውም (ከህዝቦቼ ድሃ ማለት በትንሳኤ ቀን ስግደቱን፣ ጾሙንና ዘካውን ይዞ ይመጣና ከዚያም ይህንም ሰድቦ ያንም ዘልፎ የዚህንም ገንዘብ በልቶ የዚያንም ደም አፍሶ እናም ያኛውን ሰው ምትቶ ይገኛል፡፡ በዚያን ወቅት ይቀመጥና ይፋረዱታል፡፡ ይህ ከመልካም ሥራው ይውሰዳል ያነም እንደዚሁ ያለበትን እዳ ሳይጨርስ መልካም ሥራው ካለቀ ከነሱ ወንጀል ይነሳና ወደሱ ሥራ ይደመራል በዚህም፡፡ በመጨረሻ እሳት ይዘፈቃል፡፡)

እንድሁም እንድ ቀን አገሊት በጣም ስግደት ታበዛል ጾምም፣ ምጽዋትም ነገር ግን በምላሷ ጎረቤቶቿን ታስከፋለች እንደዚሁ ተብለው ሲነገሩ ጊዜ ( እሷ የእሳት ናት፡፡) አሉ፡፡ ደግሞም ሌላዋን እገሊት ስግደቷ፣ ጾሟ፣ እንድሁም ምጽዋቷ ቀላል ነው ነገር ግን በደረቅ አይብም ቢሆን በምጽዋት ሰዎችን ትረዳለች በምለሷም ጎረቤቶቿን አታስከፋም አሏቸው ያን ጊዜ (እሷ የጀነት ናት፡፡) አሉ፡፡

አንድ ሰው ትኩረት ሊሰጠው ከሚገባው ነገር ተቀዳሚው የመጨረሻ ማማር ነው፡፡ የመጨረሻ ማማር ምስጢሩ አላህ (ዐ.ወ.) አንድን ሰው ከመሞቱ በፊት እሱን ከሚያስቆጣው ነገር ለመራቅ የሚያደርገውን ጥረት ማሰካቱ፣ ከወንጀልና ከኃጢአት እንድጸጸት ነገሮችን ማመቻቸቱ፣ ወደዒባዳና መልካም ስራ አእንዲያመራ ማገዙና ከዚያም በዚህ ሁኔታ እስከእለተ ሞቱ መዝለቁ ነው፡፡

አንድ ሰው ማንኛውም ስራው በመልካም ሥራ ላይ በመሞት መጨረሻው በማማሩ የሚወሰን መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጸውልናል፡ (ሥራዎች እኮ የሚወሰኑት በመጨረሻዎቻቸው ነው) በሌላ ሀዲስም እንድህ ብለዋል፡ (ሥራዎች እኮ ከስሩ ያለው ነገር ካማረ ያላይኛውም ያመረ አንድህም የታችኛው ከተበላሸ የላይኛውም የተበላሸ እንደሚሆን እቃ ማያዣ ናቸው፡፡)

በመሆኑም ማንኛውም ሰው መጨረሻው ያመረ እንዲሆን መጣርና በመልካም ሥራው ከአላህ (ዐ.ወ.)ጋር ለመገናኘት አስፈላጊውን ዝግጅት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (

{فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلاً صَالِحًا وَلاَ يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا}

ትርጉሙም (የጌታውን መገናኘት የሚፈልግ ሰው መልካም ሥራን ይስራ፡፡ በጌታውም መገዛት አንድንም ነገር አያጋራ..) ማለት ነው፡፡

አላህን የፈራ ለትእዛዙና ለክልከላውም የተገዛ ሰው አላህ ወደለምልካም ሥራ የሚያደርገውን ጥረት ያሳካለታል፡፡ ከዚያም በዚህ ሁኔታ እንዳለ ይሞታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ ለአንድ ሰው ደግን ነገር ሲያስብለት ያሰረዋል) አሉ ባልደረቦችም እንዴት ያሰረዋል በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ከሞት በፊት ወደመልካም ሥራ ይመረዋል) አሉ፡፡ የሐጅ ሥራ ያያዝም ሆነ ሌላው ሰው ከሐጅ ሥራ የሚቀስማቸው ሌሎቹ ትምህርቶች ደግሞ ሁሉንም ነገር ለአላህ (ዐ.ወ.) መተው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በማንኛም ዘርፍ ሰበቡን ማድርስ ግድ ሲሆን ምንም ይሁን ምንመ ግን ፈጻሚው አላህ በመሆኑ ማመን ይጠበቅበታል፡፡ አላህ የፈረደውን ነገር ማንም ሊገታው የማይችል መሆኑን በቁርኣን እንድህ በማለት አመልክቷ፡

{ وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلاَ مُؤْمِنَةٍ إِذَا قَضَى اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَمْرًا أَن يَكُونَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْ أَمْرِهِمْ وَمَن يَعْصِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ فَقَدْ ضَلَّ ضَلالاً مُّبِينًا}

ትርጉሙም (አላህና መልክተኛውም ነገር በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ለነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይደባም፡፡የአላህንና የመልክተኛውን ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነንን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡) ማለት ነው፡፡

{مَّا يَفْتَحِ اللَّهُ لِلنَّاسِ مِن رَّحْمَةٍ فَلَا مُمْسِكَ لَهَا وَمَا يُمْسِكْ فَلَا مُرْسِلَ لَهُ مِن بَعْدِهِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}

ትርጉሙም (አላህ ከችሮታ ለሰው የሚከፍታት ለእርሷ ምንም አጋጅ የላትም፡፡ የሚያግደውም ለርሱ ምንም ለቃቂ የለውም፡፡ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

{وَإِن يَمْسَسْكَ اللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُ إِلَّا هُوَ وَإِن يَمْسَسْكَ بِخَيْرٍ فَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ وَهُوَ الْقَاهِرُ فَوْقَ عِبَادِهِ وَهُوَ الْحَكِيمُ الْخَبِيرُ}

ትርጉሙም (አላህም በጉዳት ቢነካህ ለርሱ (ለጉዳቱ) ከእርሱ በስተቀር ሌላ አስወጋጅ የለውም፡፡ በበጎ ነገር ቢነካህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ሁሉንም ነገር ሙሉ ለሙሉ ለአላህ (ሱ.ወ.) መተው የምሉእ እምነት ምልክት የእስልምና መሰረት መሆኑን ሊቃውንት አመልክተዋል፡፡ ይህም እውን ይሆን ዘንድ አንድ ምእምን በአላህ ላይ ያለው ግንዛቤ ምንግዜም መልካም መሆን አለበት እንድሁም አላህ በከተበለት መርካት ይኖርበታል፡፡ እንደዚህ ከሆነ ያሰው በልዩ እርካታ በመረጋጋትና በደህንነት ይኖራል፡፡

ህንነ ቃሌን ተናገርኩኝ ለኔና ለናንተ ከአላህ ዘንድ ምህረትን እጥይቃለሁ፡፡

*  *  *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላከተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የሐጅን ሥራ ያጠናቀቀው ሰው በአላህ ፈቃድ ከሱ ከፈጣሪው ምህረት የተቸረው ሆኖ ተመለሰ ስንል ከዚህ ላይ ሰዎች በሚሰነዘሩት ሞገስና የማሞካሸት ቃል ከመሸንገል ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያፈርግ ይገባል፡፡ ሐጅ አንድ ሰው የሚያገኘው ማእረግና ከሰዎች መካከል የመፎካከሪያ ሥራ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህ ሰው ወደሀገሩ ከተመለሰ በኋላ ራሱን ዝቅ አድራጊና ፈሪሃ አላህ ሊሆን ይገባል፡፡ ሐጅ ታላቅ ደረጃ ያለው ግዴታ እንድሁም ታላቅ ምንዳ ያለው ዒባዳ ሲሆን ችግሩን ሁሉ ተጋፍጦ ያከናወነው ሰው በልቡ ልዩ ጣእሙን ያገኛል፡፡ ለአላህ ብሎ በሚያደርገው ራስን ዝቅ ማድረግ በሕይወቱ ተጽዕኖው ጎልቶ ይታያል፡፡ በመሆኑም በነፍስያው ምንም ዓይነት ትእቢት አይገባም የአላህ ዒባዳውንም መደነቅ የሚባል ተንኮል አይጋፋውም፡፡ አንድ ምእምን በአምነትና በእውነተኛ ልቦና አንድ ዒባዳ የሚሰራ ከሆነ ወደሌላ የበለጠና የላቀ ዒባዳ የሚያሻግር መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከዚያም ከዒባዳ ወደዒባዳ ያለማቋረጥ የሚሸጋገር ይሆንና ወደመልካምነት ደረጃ ያድጋል፡፡ ይህ ታድያ ዒባዳው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የአነዚያ ወደመልካም ሥራ የሚቻኮሉት ሰዎች እምነት በፍርሃት የተሞላ እምነትና ምንዳ ለማግኘት ተስፋ ያደረገ እምነት መሆኑን እንድህ በማለት ገልጧል፡

{إِنَّ الَّذِينَ هُمْ مِنْ خَشْيَةِ رَبِّهِمْ مُشْفِقُونَ *وَالَّذِينَ هُمْ بِآيَاتِ رَبِّهِمْ يُؤْمِنُونَ *وَالَّذِينَ هُمْ بِرَبِّهِمْ لَا يُشْرِكُونَ*وَالَّذِينَ يُؤْتُونَ مَا آتَوْا وَقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَى رَبِّهِمْ رَاجِعُونَ*أُولَئِكَ يُسَارِعُونَ فِي الْخَيْرَاتِ وَهُمْ لَهَا سَابِقُونَ}

ትርጉሙም (እነዚያ አርሱን ጌታቸው ከመፍራታቸው የተነሳ ተጨናቂዎች የሆኑት፡፡ እነዚያም እነርሱ በጌታቸው ታእምራት የሚያምኑት፡፡እነዚያም እነርሱ በጌታቸው (ጣዖትን) የማያጋሩት፡፡ አነዚያም የሚሰጡትን ነገር አነረሱ ወደጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡት፡፡ እነዚያ በመልካም ሥራዎች ይጣደፋሉ፡፡ አነርሱም ለርሷ ቀዳሚዎች ናቸው፡፡) ማለትነው፡፡

ኢብን ከሲር የተባሉት የቅዱስ ቁርኣን ተንታኝ ‹እነሱ መልካም ሥራ ከመስራታቸውና ከእምነታቸው ጋር አላህን ይፈራሉ ሁኔታቸውም እንዳይለወጥ ይጨነቃሉ ማለት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡› (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ ብለዋል፡

‹አንድ ቀን ነብያችንን እንድህ በማለት ጠየቅሁኝ፡፡ የአላህ መልክተኛ ሆይ እንድህ የሚለው የአላህ (ዐ.ወ.) ቃል፡

{وَالَّذِينَ يُؤْتُونَ مَا آتَوْا وَقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَى رَبِّهِمْ رَاجِعُونَ}

ትርጉሙም (እነዚያም የሚሰጡትን ነገር እነርሱ ወደጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡት፡፡) ማለት ነው፡፡

ያን አላህን እየፈራ የሚሰርቀውን፣ ዝሙት የሚፈጸመውንና የሚየስክሩ ነገሮችን የሚጠጣውን ሰው ማለት ነውን? ስል ጠየቅሁኝ፡፡ እሳቸውም (አንች የአቡበከር ልጅ አንች የሲድቅ ልጅ ሆይ! ነገሩ እንደዚህ አይደለም ነገር ግን ያንን አላህን እየፈራ የሚሰግደውን፣ የሚጾመውንና መጽዋት የሚሰጠውን ማለት ነው፡፡) አሉ፡፡ አንድ እውነተኛ ምእምን ዒባዳውን ከማብዛትና የትርፍ ዒባዳ ከመጨመሩ ይልቅ ያ የፈጸመው ጥቂት ዒባዳ ተቀባይነት አገኘ አላገኘ እንድሁም በዚህች ዓለም ህይወቱ ተጽእኖ አሳድሯል ወይስ ምንም ምልክት የለውም ለሚለው ጉዳይ የበለጠ ትኩረትይሰጣል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) በአላህ ዒባዳና ትእዛዙን በመፈጸም ዘርፍ ጥረት እንዲያደርጉ እንድሁም ማንኛውንም መልካም ሥራ ጥቂት ነው ብለው እንዳይተውና ዒባዳንም አብዝተው በዚያ የኢባዳ ብዛት የመደነቅ ችግር እዳይደርሰባቸው አዟል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በራሱ መልካም ሥራ መደነቅ አጥፊና ሥራን ከንቱ የሚያስቀር መሆኑን አስጠንቅቀዋል፡፡ (ከራሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዓባስ እንድህ አሉ፡ ‹የአላህ መልክተኛ እንድህ ብለዋል፡ (አጥፊ ነገሮች ሦስት ናቸው፡ -እነሱም- አንድ ሰው በራሱ መደነቁ፣ ባለቤቱ የሚገዛለት ስስትና ባለቤቱ የሚከተለው የመንፈስ ፍላጎት ናቸው፡፡)›

ጌታችን ሆይ! አንትን ማስተወስና ማመስገን እንድናበዛ እንድሁም ዒባድነችን እንዲያምር አንተው እገዘን፡፡ በመልካሙ ታዛዥነትና ዒባዳም ቀጥ ማለትን አሳካልን፡፡ አሜን፡፡